## ከኢትዮሚዲያ ርእሰ አንቀጽ

# ከንቱ ውዳሴ

(ትርጉም መላኩ ፀጋዬ መኮንን)

የሚያዚያ 2000 ዓ.ም ‘‘ምርጫ’’ የማያረካና ትርጉም የለሽ ሆኖ ተጠናቋል። ለእይታ ብቻ የታለመ ምርጫ ተካሄደ። ለተወሰኑ ቀናት ግን ገዝዎቹ የምስራች እንድንላቸው የሚያስችል ሁኔታ ፈጠሩ እርስ በእርሳቸው“የኢትዮጵያ የዲሞክራሲ ሂደት ማንም ሊያቆመው የማይችል” መሆኑን የሚገልፁበት የባዶ መፈክር ቀናት አመቻቹ። የሚደንቀው ግን በዚህ አመት ምህረት “ምርጫ” መካሄዱን ከሳምንት በኃላ ማንም እራሱ የሚያስታወስ አለመኖሩ ነው።

ለምንድን ነው “ምርጫው” ትርጉም የለሽና ለይስሙላ የተካሄደ ነው የምንለው? ምክንያቱም ማንም “የምርጫውን” ምንነት አያውቅም። ኢትዮጵያውያን አያውቁቱም። ሌላው ይቅርና አስፈፃሚ ሆነው ምርጫው እንዲታመንላቸው በየደረጃው የተሰለፉትም ጋሻ ጃግሬዎች ቢሆኑ አያውቁቱም። በመሆኑም ለአንባቢያን ቀላል ጥያቄዎች እንጠይቅ፤

“ምርጫው” በሀገሪቱ የደረሰውን የገበያ ንረትን፤ የምግብና የነዳጅ ዋጋ ማሻቀብን፤በከፍተኛ ደረጃ መጨመርንና የኢኮኖሚ ውድቀትን ብሎም በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ በድህነት እየማቀቀ በሚኖርበት ሀገር ይህን ተጠቅመው የግል ሀብት የሚያግበሰብሱትን የሚመለከት ነው?

ወይስ የሚበላው አጥቶ በጉጉት የእለት ጉርሱን የሚጠብቀውን አንድ አምስተኛው የሚሆነው የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚመለከት ነው? ወይስ ይህን ድርቅ በችልታ በመመልከት በተጎጂዎቹ ስም የሚመጣውን የዓለም ሕብረተሰብ እርጥባን ከዚህ በፊት እንዳደረጉት ሁሉ በባለሙያዎቻቸው አማካኝነት ተጠቅመው ሀብት ማግበስበሻ ለማድረግ በመያዛነት ስለሚጠቀሙበት ሁኔታ ነው?

ወይስ መለስ ስለሚያካሂደው ብሄራዊ ምዝበራ፤ በሀገራቱ ሀብት ላይ ስለሚደረግ ዘረፋና ስርቆትት ማስቆምን የተመለከተ ነው? ወይስ በአጠቃላይ ተጠያቂነት በጎደለው ሁኔታ የሚካሄደውን ሀገራዊ የሀብት ማራቆት ተግባር የሚቆምበትን ሆኔታ ላይ የተነጣጠረ ነው?

ወይስ በጠራራ ፀሃይ ከብሄራዊ ባንክ ያለምንም ተቆጣጠሪ እየወጣ ደብዛው እንዲጠፋ ተደርጎ በሚሰወረው የወርቅ ስርቆት ጉዳይ ላይ ነው?

ወይስ 20 ከመቶ ሴቶችና 33 ከመቶ ወንዶች ልጆች የትምህርት እድል የሚያገኙት ቁጥር ስለሚጨምርበትና በዓለም ዝቅተኛ የትምህርት ስርዓት ስለሚሻሻልበት ሁኔታ የዳሰሰ ነበርን?

ወይስ በዓለም የከፋ መሰረታዊ የጤና ስርዐት ስለስፈነበት (20 ከመቶ ኢትዮጵያውያን ብቻ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት የተዳረሰበትን፤ አንድ ሀኪም ለ40,000 ሕዝብ፤ አንድ ነርስ ደግሞ ለ14,000 ሕዝብ አገልግሎት ስለሚሰጡበት ሁኔታ ያተከረ ነበርን?

ወይንስ ሕዝብ የተጣራና ንፁህ የመጠጥ ወሃ ስለሚዳረስበት ሁኔታ የተመለከተ ነው /24 ከመቶ ብቻ ንፁህና የተጣራ ዉሃ ያገኛሉ/?

ወይስ ማቆሚያ ከሌለው የሶማሌ የጎላ ብጥብጥ የኢትዮጵያ ጦር ስለሚወጣበት ብሎም የሀገራቱን ብሄራዊ ሀብት እየሟጠጠና አያሌ ወጣቶች ሕይወት በመቅጠፍ ላይ ስለአለው በአሳፋሪው የሶማሊያ ወረራ ጉዳይ ላይ የተመለከተ ነው?

ወይም በግፍ አገዛዙ የሚያደርሰውን የሰብአዊ መብት ረገጣና እና ሕገ መንግሥቱንና የሕግ የበላይነትን አለማክበሩን የሚመለከት ነው?

እውን "ምርጫው" በሀሳቦች ልዩነት ላይ ያነጣጠረ ለኢትዮጵያና ለሕዝብ የወደፊት ራኢባላቸው አመለካከት ላይ ያነጣጠረ ነበርን?

በእውነት ኢትዮጵያ አሁን ያጋጠሟትን ችግሮችና የወደፊቱንስ የተመለከተ ነበርን?

"ምርጫው" የመለስ የሀገር ዓቀፍ ተቋማት በሚፈጽሙት ጥፋት ላይ የታለመ ሕዝበ ውሳኔ ነበርን?

የኢትዮጵያ ሕዝብ እውነተኛ ስሜቱን የሚገልጽበት፤ ሀቀኛ መሪዎቹን የሚመርጥበት ብሎም የእነርሱን የወደፊት እውነተኛ ስሜትና አመለካከት የሚያንፀባርቅ ነበርን?

በማጨረሻ "ምርጫው" ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም የሚጠቅም ነገር የለውም። ለዚህም ነው ሁሉ ነገር ትርጉም የለሽ የማስመሰያ ሂደት ነው የምንለው።

ይህ ብቻ ግን አይደለም "ምርጫው" ትርጉም የለሽ ነው የምንለው፤ ሌላው ጉዳይ ዉጤቱ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ አንድ ሽርፋ እህል አይጨምርም። እንደገናም ለአንባቢዎቻችን ቀላል ጥያቄዎች እናቅርብ ። እውነት የአገዛዙ "ምርጫ" ማሸነፍ ወደ ሚከተሉት ጉዳዮች ያመራል /ይወስደናል/?

- ያለፍርድ ሂደት የታሰሩ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ የፓለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ ያደርጋል?
- ገዳዮች፤ ገራፊዎች እና የሰብአዊ መብት የሚጥሱ ለፍርድ ይቀርባሉ? በሀገራችን የሕግ የበላይነት ይመሰረታል?
- የሀገሪቱ ሕዝብ መሰረትታዊ የምግብ አቅርቦትን ለማሟላት የሚያስችል የግብርና ስርአት እንዲኖር ያደርጋል? እንደዚሁም የነዳጅንና የምግብ ዋጋ እንዲቀነስ ያስችላል?
- የሰብአዊ መብትንስ ያከብራል ?"ሕገ መንግስታዊ"መብቶችን" ይጠብቃል?
- ነፃ የሆነ የፍትህ አካል ማቋቋምና ፍትህ አግባብ ያለው እንዲሆን ያስችላል?
- የመናገር ነፃነትንና የነፃ ፕሬስ እንዲጠበቁ ያስችላል? ብሎም ነፃ ጋዜጠኞችን ይፈታል?
- የሕዝባዊ ማህበራትን በነፃ እንዲቀሳቀሱ ሁኔታዎችን ያመቻቻል?
- የተሻለ የትምህርትና የጤና አገልግሎት ዜጎች እንዲያገኙ ያስችላል?
- ከሶማሊያ ጦሩ እንዲወጣ የሚያስችል ሁኔታ ይፈጥራል?

"ምርጫው" በኢትዮጵያ ሕዝብ ሕይወት ላይ የሚፈይደው አንዳችም ነገር እንደሌለ እናምናለን ።ለዚህም ነው የሚያዚያ 2000 ዓ.ም የኢትዮጵያ ምርጫ እርባነቢስ እና ከንቱ ውዳሴ ነው የምንለው። የ2000 ዓ.ም፡ ምርጫ ትልቅ ባዶ ምርጫ ነበር፡ ምክንያቱም "ምርጫው" ምንም ነገር የሌለውና ዳግማዊ የማጭበርበሪያ ምርጫ በመሆኑ እናወግዘዋለን! የተጋነነ፤ የፌዝና የቀልድ ዲሞክራሲ እንደሆነና በዲሞክራሲ መርሆዎች ላይ የተቃጣ አሳፋሪና ማስመሰያ ብሎም በሕዝባዊ ሉአላዊነት ላይ የተካሄደ ጥቃት በመሆኑ እንቃወመዋለን።

የግንቦት 1997 ምርጫን ስንመለከት እውነተኛ ምርጫ ነበር። ይህን ስንል ምን ማለት እንደሆነ እውነቱን የመግለጽ ድርሻ አለብን። በተለያዩ ወቅቶች "ምርጫዎች" ነበሩ። በ1997 ምርጫ ነበር ይህ ምርጫ ግን እውነት ነበር የግንቦቱ 1997 ምርጫ ትክክለኛ የነበረው የተለያዩ ሀሳቦችን ያስተናገደ በሀሳብና በወደፊት ራኢዎች ላይ ያነጣጠሩ ጠንካራ የአመለካከት ወድድሮች ነበሩበት። ምርጫው በመለስ /የኢህአዴግ/ አገዛዝ ላይ መሰረታዊ ሕዝበ ውሳኔ የተሰጠበትም ነበር። ብቸኛው ጥያቄ ከድምፅ አሰጣጡ በፊት የነበረው "መለስንና የወሮ በላ የግብረ አበሮቹን ወንጀለኛ ቡድን በስልጣን ላይ እንዲቀይ ትፈልጋላችሁ?" የሚል ነበር። ስለዚሁ ጉዳይ ሕዝቡ የሰጠው ምላሽ አይሆንም! በቃ!በቃ! ይበቃናል የሚል ነበር።  ይኸውም መልስ በግልጽ በመላ ዓለም ተሰራጨ፤ተደመጠ።

የ1997 ምርጫ እውነት ነበር። ምክንያቱም ጠንካራ የተቃዋሚ ፓርቲዎች በምዝበራ ላይ ያለውን አገዛዝ ከአመት አመት ማዝቀጥ በማስረዳት የተፎካከሩበት ነበር። በጋዜጦች፤ በራዲዮ እና ቴሌብዥን በመሳሰሉት የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙሀን ግልፅና ነፃ የሆነ ውይይት ተካሂዷል። ነፃ ፕሬስ አምባገነኖችን ተጋፍጧል። የሕዝባዊ ማህበራት አመራሮች መራጩን ሕዝብ ስለምርጫው ድምፅ አሰጣጥ በማስተማር ብርቱ ጥረት አድርገዋል። መራጮች በግልፅ እና ያለምንም ፍራቻ በሕዝባዊ ስብሰባዎች ላይ በስርአቱ ላይ የተሰማቸውን ቅሬታና ለአገዛዙ ከበሬታ የሌላቸውና ፍሬቢስ ስርአት መሆኑን ገልፀዋል። በመጨረሻም ተቃዋሚዎች በምርጫው አሸነፉ። የቅንጅት ጠንካራ አባላት እንዳልባሌ ነገር እንዲገለሉ ተደረገ። የ1997 ምርጫ ደስ የሚለው ነገር በግንቦት 7 ቀን ድምፅ ሰጭዎች በኢትዮጵያ የተመዘገበ ታሪክ ውስጥ ተሰርቶ የማያውቅ ታሪክ ሰሩ። የሀገራችን ጉድፍ ለማፅዳት ዲሞክራሲን ተጠቀሙ፤ የምርጫ ማጽጃቸውን አንስተው ለ15 አመታት የተካበተውን የተበላሸ አሰራር አፀዱት። ይህ የእውነተኛ ምርጫ ማረጋገጫ ያረጋገጠና ትምህርት ሰቶ  ነበር።

የእመኑልኝ ጨዋታ ይብቃ። እውነትን መጋፈጥ እንገደዳለን። የአገዛዙ ቀዳሚ ተልዕኮ እውነተኛን ምርጫ  አመራር መስጠት ቀርቶ፤ የእመኑልኝን ምርጫ እንኳ መምራት አለመኣሉ ነበር። ዋናው ተልእኮው ስልጣኑን በምንም መንገድ ተጠቅሞ ማቆየት ነው። ይህን ለማድረግ ተቃዋሚዎችን ማዳከምና፤መከፋፈልና መበተን አለበት። የበሬ ወለድ   ምርጫ በማካሄድ አገዛዙ ሕዝቡንና  የተቃዋሚ ፓርታዎችን ሀገሪቱ በገጠማት ማህበራዊና ኢካኖሚያዊ ሁኔታ እንዳይሳተፉ ማምታታት እንደዚሁም  እርባና ቢስ በማድረግ በአንፃሩ ከዓለምዓቀፍ ለጋሽ ማህበረሰብ ለሕዝብ የሚሰጠውን ምፅዋት ለመዝርፍ አመች ሁኔታዎችን መፍጠር ነው።

በተመሳሳይ ሁኔታ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉ ጥቂት የፖለቲካ ድርጅቶች በስጋትም ይሁን በሌላ ሁኔታ የተነሳ ለአገዛዙ የሚያመች ስራ ለመፈፀም ከተስማሙ በኃላ ከምርጫው መጨረሻ ሰዓት ላይ ወይም "ምርጫው" የመጀመሪያ ምእራፍ ላይ ጥለው የመውጣታቸው ምክንያት "ሁሉም የምርጫ ሂደቱ ሕገወጥ መሆኑን በመገንዘብ" ወይንም ከምርጫ እራሳቸውን በማራቅ "ከአገዛዙ ጋር ተባብረው ለመስራት የማያስችል ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ለአለም ህብረተሰብ ለማስወቅ" ወስነዋል ማለት ነዉ።

ምንም ጥርጥር የለውም አገዛዙ የነዚህን የተቃውሞ እርምጃ ለማጣጣልና በቀለጠፈ መንገድ ለአለማቀፍ ህብረተሰብ ለማሳወቅ የሚከተሉትን ቅስቀሳዎች ይጠቀማል። አንዳንድ ጠቃሚ “ተቃዋሚው” ጎራ ያሉ ሀይሎችም ሳይቀሩ ሁኔታው ተምታቶባቸዋል ወይም ጉዳዩን በብስለት ምን እንደሚፈልጉ አልተገነዘቡም በማለት በባህሪያቸው ወሳኝነት እንደሚያንሳቸው በመግለፅ ያጣጥላቸዋል፤ ይህ ቅስቀሳ በተወሰነ ተቃዋሚዎች ላይ በሰፊው ሲነገር የቆየ ነው።

ለሁሉም የዲሞክራሲ አፍቃሪ ኢትዮጵያዊያን ኃይሎች በንቃት የአገዛዙን የምርጫ ቀልድ ለመታገል ጊዜው አሁን ነው። አሁን የመለስን አባገነናዊ አገዛዝ ለመታገል ከብሄረሰብ፤ ከፖለቲካ እና ከርዕዮተ ዓለም አመለካከት ልዮነት ባሻገር መረዳት ያለብን በከፍተኛ ጥረትና ህብረት አንባገነኑ በተፅዕኖ እንዲገለል ጫና መፍጠር አለብን በቅርቡ በሰብአዊ መብት ትግሉ ዙሪያ ሕብረት መስርተን በጋራ መንቀሳቀስ እንዳለብን ጥሪ ቀርቧል። እንደዚህ አይነትን ጥረት በሙሉ መደገፍ አለብን ምክንያቱም የፍትህ የእኩልነት እና የዲሞክራሲ መሰረቱ ሰብአዊ መብቶችን መከበር ነው።

ከዚህ ሁሉ በኃላ ስለመለስ “ምርጫ” ስራ መልፋት የለብንም። ለመይረባ ነገር ከንቱ ውዳሴ ነው። መለስም ሆነ እኛ እናውቃለን “ምርጫ” በሙሉ እመኑልኝ የድራማ እቃቃ ጨዋታ፤ የማሽሟጠጥ፤ የማታለል ነው። ከሁሉ ነገር መለስ በሚያዚያ ምርጫ ያዘጋጀው ኢትዮጵያውያን ሁሉ ለዘገየው /የአፕራል ዘፋል/የቀልድ ቀን እንኳን ደስ ያላችሁ ብሎ የቀለደብንና እያሾፈብን መሆኑን ሲያሽሟጥጥብን ነው።